# አሰልጥኖ መስጠት!

ከወጨፎ ኖርዌይ

አንድ ህንድና አንድ ፓኪስታን ጎረቤታሞች ሆነው ጎን ለጎን ያለ ቤት ይዘው ይኖሩ ነበር። ህንዱ አንድ ዶሮ የነበረችው ሲሆን ጠዋት ጠዋት እየተነሳ ከራሱ ግቢ ውስጥ ዶሮው የምትጥለውን እንቁላል እየለቀመ ቁርሱን የእንቁላል ጥብስ መብላት የለመደ ስለነበር አንድ ቀን እንደወትሮው ዶሮው እንቁላል ወደምትጥልበት የራሱ ግቢ እንቁላል ለመልቀም ሲወጣ ዶሮው ከፓኪስታ፦ ግቢ ሄዳ እንቁላል ስትጥል ይመለከታታል፤ ወዲያውም በመሮጥ ወደ ፓኪስታ፦ ግቢ እንቁላሉን ለመውሰድ ሲሮጥ ፓኪስታ፦ እንቁላሉን አፈፍ ሲያደርግ ይመለከታል፣ ህንዳዊውም ዶሮዋ የኔ ሰለሆነች እንቁላሉም የኔ ነው አምጣ ማለት፤ ፓኪስታ፦ ደግሞ ዶሮዋ ያንተ ብትሆንም እንቁላሉን የጣለችው ከኔ ግቢ ውስጥ ስለሆነ እንቁላሉ የሚገባው ለኔ ነው ማለት።

ይህ ሁኔታ በእኛና በዛሬዋ ጎረቤታችን ቀድሞ ደግሞ ሀገራችን በነበረችው ሀገራችን ኤርትራመካከል ያለውን የይገባኛል ክርክር ቀልድ ያስታውሰናል።ወያኔ ከሻብያ ጋር በነበረው የጫካ ፍቅር የኤርትራ ጥያቄ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው በማለት ጠሩንና ጭፍራውን ጭምር በማሳመን ሀገራችንን አስገንጥሎ ከመስጠት ባሻገር የቀራትንም መሬቶች በሰበብ አስባቡ እየሸነሸነ ለሱዳንና ለኤርትራ መስጠቱ ሳያንስ፤ የስንት ሺ ህ ደም የፈሰሰባትንና በሰራዊታችን አኩሪ ተጋድሎ የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ የተውለበለበባትን ባድመ በፍርድ ቤት ውሎ በመረታት አሰረክቦ ከመጣ በሁዋላ ደስ ይበላችሁ ባድመና አካባቢዋ ለኢትዮጵያ ተወስኖላታል ከጠየቅነው በአብላጫው ለኛ ተፈርዷዋል በማለት ቁጭ በሉው መንግስት ቁጭ ሊያደርገን ያሰበው ቅጥፈቱ ጊዜ መጥቶ በጊዜ ተገልጥጦበታልወያኔዎች የስልጣን ዘመናቸውን ለማራዘም የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም። አንድ ዘመን ብፅአትና አበበ፣ የተባሉ ከያንያን እየተቀባበሉ የሚዘፍ፦ት ዘፈን ትዝ አለኝ፣ ግጥሙንናስንኙን አሁን ማስታወስ ባልችልም፤ አሰልጥኖ መስጠት፣ የሚል አንድ ሀረግ እንዳለው ግንትዝ ይለኛል። ሩህ፣ የተባለው ጋዜጣ በግንቦት 8፣ 1995 ሀተታው ላይ በባድመ ግዛት ውስጥ ከ 8 ሚሊዮን ብር በሚበልጥ በጀት ሰፊ የልማት ስራ እየተከናወነ መሆ፦ን አስተዳዳሪዎችዋን እንደ ዜና ምንጭ በመጠቀም ያወጣው ዜና 400 አዳዲስ መስሪያ ቤቶችና ሁለት ትምህርት ቤቶች ተገንብተው ማለቃቸውን ጭምር  በዜናው ላይ አስፍሮዋል። እንግዲህ ልብ በሉ፣ ይህ ሁለት አይነት ጨዋታ ያለው ይመስላል፤ በአንድ በኩል ባድመየኛ ስለሆነች የትግራይ ህዝብም ሆነ የኢትዮጵያ ህዝብ አትጨነቅ እየገነባንልህ ነው በማለት ቁጣ ለማብረድ የምትሰራ ሴራ ስትሆን፤ እድሜን ለማሰንበት፣ በሌላ በኩል ደግሞእነ ብፃይ መለስ፣ ለናቶቻቸው ሀገርም ቢሆን ማሰባቸው አልቀረምና እየገነቡ መስጠት ወይም አሰልጥኖ መስጠት የሚለው መፈክራቸው እንደተጠበቀ ሆንዋል ማለት ነው። ለመሆ፦ በጦርነት ያሸነፈች ሀገር መሬትዋን ከያዘች በሁዋላ ለፍርድ ድርድር ራስዋን ያቀረበች፣ የራስዋን ጥቅም በሚያሳጣ ስምምነት ይግባኝ የሌለው የፍርድ ውሳኔ እስከመጠየቅ የደረሰች ሀገር በአለም ላይ ከኢትዮጵያ በስተቀር ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?

ማሰርያው እንደ ፓኪስታ፦ እና እንደ ህንዱ ቀልድ ሊሆን ነው፤ ህንዱ አይ እንግዲህ ፍርድ ቤት ከመሄድ በራሳችን የግልግል ዳኝነት እንፍታው ይለዋል፤ ፓኪሱም ይስማማል። ህንዱ፣ እንግዲህ በመንደርደር ወደሁዋላ በመሄድ ተራ በተራ በካልቾ እንመታታ፤ በካልቾየተመታው ሰው ከ30 ደቂቃ በላይ ራሱን ከሳተ ተሸናፊ ይሆናል ይለዋል፣ ሁለቱም በዚህተስማምተው ፍልሚያውን ይጀምራሉ። ህንዱ ወደሁዋላ በመንደርደር ራሱን በማዘጋጀትባለ በሌለ ጉልበቱ ፓኪስታ፦ን ቢያጦዘው፣ ፓኪስታ፦ ለተወሰነ ደቂቃ ራሱን

ስቶ ይወድቃልከዚያም ወደ ህባራዊ-ህሊናው ሲመለስ፤ በል! አሁን ደግሞ የእኔ ተራ ነው ቢለው፤ አያ ህንድ ሆዬ፣ ` ይቅርብኝ እንቁላልህን ይዘህ ሂድ’ አለው እንደተባለው፤ በፍልሚያ ያሸነፈው ሀገር መሬቱን በገፀ በረከትነት መስጠቱ እጅግ አስገራሚው ነገር ነው፤ አሰልጥኖለእናት ሀገር መስጠት ይሉዋል ይሂ ነው።